የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ በኅብረቱ 32ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአስተምህሮ ዝንፈቶች፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆኑ ልምምዶች እና በሞራል ውድቀቶች ላይ የወጣ የአቋም መግለጫ

መግቢያ
እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች አገራችን ኢትዮጵያ ከመጀሪያዎቹ መቶ ዓመታት ጀምሮ የወንጌልን እውነት የተቀበለች አገር መሆኗን እናውቃለን። በተለይም ደግሞ፥ ካለፈው አንድ ምእተ ዓመት ገደማ ጀምሮ እግዚአብሔር በምድራችን ያደረገውን ድንቅ የወንጌል እንቅስቃሴ እናደንቃለን። በዚህም እንቅስቃሴ ሚሊዮኖች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ፈልሰዋል፤ የብዙዎች ሕይወት ተቀይሯል፤ እጅግ ብዙዎች ከተለያዩ እስራቶች ተፈትተዋል፤ ከአምላካችንም የምሕረትና የርኅራኄ እጅ ብዙዎች ፈውስን ተቀብለዋል። ዛሬም፥ እግዚአብሔር አምላክ በቅዱስ መንፈሱ አማካኝነት ብዙዎችን ወደ መንግሥቱ እያፈለሰ፥ ድንቆችንና ታምራቶችን እየሠራ ብዙዎችን ከእስራት እየፈታ እንደሆነ ምስክሮች ነን። ለዚህ ሁሉ ክብሩን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር እንሰጣለን!

እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች፥ “ወንጌላውያን” ያሰኙን፥ መሠረታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑና በርቱእ ክርስትና ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው አስተምህሮዎች አሉን። ከሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርእቱእን ታሪካዊ የክርስትና እምነት መግለጫዎች ማለትም የሐዋርያት፥ አትናቴዎስ፥ ኒቂያ፥ ኬልቄዶን ጋር ተያይዞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የእምነት አቋም እንቀበላለን።

በእስትንፋሰ መለኮት የተጻፉትን 66ቱን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ስሕተት አልባነት፥ ተአማኒነት፥ ብቁነት እና በእምነትና በተግባር ላይ፥ እንዲሁም በሥርዐተ አምልኮ ሁሉ ላይ ያላቸውን የበላይ ባለሥልጣንነትና ዳኝነት፥ ራሱን በሦስትነት የገለጠ አንድ እውነተኛ ሕያው አምላክ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ መኖሩን፥ የሕያው እግዚአብሔር አንድያ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መኾኑን፥ የእኛ ምትክ ሆኖ ለኀጢአት ስርየት በመስቀል ላይ መሞቱን ከሞትም በአካል መነሣቱን፥ በዓለም ፍጻሜም ዳግም የሚመለስ መኾኑን፥ አካላዊ መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ፥ ከአብና ከወልድ ጋር የተካከለ አምላክ መሆኑንና አማኞችን በኀይል በመሙላትና እንደ ፈቃዱም የጸጋ ስጦታዎችን በማደል ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጽና ለአገልግሎት የሚያሰማራ መሆኑን፥ ድኅነት በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የሚገኝ መኾኑን፥ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የኀጢአት ስርየት ያገኙ እውነተኛ አማኞችን ሁሉ የምትይዝ አንዲት የክርስቶስ አካልና የእምነት ማኅበረ ሰብ መሆኗን፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ለስብከተ ወንጌል ጥሪና ተግባር ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን እናምናለን።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት 32ኛ መደበኛ የጠቅላላ ጉባኤ በአስተምህሮ መዛነፎች ላይ፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆኑ ልምምዶች እና የሞራል ውድቀት ጉዳዮች ላይ የቀረቡትን የጥናት ወረቀቶች ካደመጥንና ከተወያየን በኋላ፥ ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ከመገንዘባችን በላይ፥ አፋጣኝ መፍትሔ ካልተሰጠው የክርስትናን መሠረታዊ ይዘት የሚያፋልስ፥ የመንፈስ አንድነታችንን የሚያናጋ፥ የወንጌልን ግስጋሴን የሚገታ ትልቅ አደጋ እንደተጋረጠብን ታይቶናል። በመሆኑም፥ የሚከተለውን ባለ 10 ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተናል።

1. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ “የእምነት ቃል እንቅስቃሴ” ተብሎ በሚጠራው የስሕተት ትምህርት ላይ ያለንን ጽኑ ተቃውሞ እንገልጻለን፤ አስተምህሮው “ሰው መንፈስ ነው፥ ነፍስ አለው፥ በሥጋ ውስጥ ይኖራል” ማለቱን፥ “እኛ እና አብ አንድን ነን” ማለቱን፥ “እኛ እና ክርስቶስ አንድን ነን” ማለቱን፥ “እኛ ትንንሽ አማልክት ነን” ማለቱን፥ “ክርስቶስ ሰይጥኗል” ማለቱን፥ “እኛ ካልፈቀድንለት በስተቀር እግዚአብሔር በምድር ላይ መሥራት አይችልም፤ ሕገ ወጥ ይሆናል” ማለቱን፥ “የእኛ እምነት እንደ እግዚአብሔር ያለ እምነት ነው” ማለቱን፥ “በሥጋ የሚሠራ ኀጢአት ችግር የለውም” ማለቱን፥ “የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ለኀጢአት ስርየት በቂ አይደለም” ማለቱን እና ሌሎች መሰል ትምህርቶቹን አጥብቀን እየተቃወምን፥ እነዚህ አስተምህሯዊ አቋሞች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከተመሠረተው የወንጌላውያን ክርስትና አስተምህሮ ጋር ፍጹሞ የሚቃረኑና የማይወክለን መሆኑን እንገልጻለን፤

2. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ “የብልጽግና ወንጌል” ተብሎ በሚጠራው የኑፋቄ (የስሕተት) ትምህርት ላይ ያለንን ጽኑ ተቃውሞ እንገልጻለን፤ አስተምህሮው፥ “አማኞች ፍጹም ሊታመሙ አይችሉም” ማለቱን፥ “አማኞች ፍጹም ሊደኸዩ አይችሉም” ማለቱን፥ “ሰዎች የሚታመሙትም ሆነ የሚደኸዩት

ከእምነት ዕጦት የተነሣ ነው” ማለቱን፥ “ከአንደበታችን የሚወጣው ቃል ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል የመፍጠርና የማድረግ ጉልበት አለው” ማለቱን እና “የክርስቶስን መስቀል ምሳሌያዊ ጥሪ አንቀበልም” ማለቱን እና መሰል ትምህርቶቹን አጥብቀን እየተቃወምን፥ እነዚህ አስተምህሯዊ አቋሞች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከተመሠረተው የወንጌላውያን አስተምህሮ ጋር ፍጹሞ የሚቃረን እና እኛን የማይወክለን መሆኑን እንገልጻለን፤

3. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም ባለሥልጣንነት በቃልም ሆነ በተግባር የማይቀበሉትን፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙላት የማይቀበሉትን፥ የክርስቶስን ፍጹም መለኮትነት እና ሰውነት በማይነጣጠል፥ በማይከፋፈል እና በማይለዋወጥ አንድነት መኖሩን የሚክዱና የሚበራርዙ ትምህርቶችን፥ በስጦታዎች ላይ መበላለጥን፥ የሎሌነትን መንፈስ የሚጻረር የግለ ሰብ ግነትንና ማእከልነት እና ጤናማ ያልሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎምን የሚያራምዱትን እንቃወማለን፤ የማይወክሉን መሆኑንም እንገልጻለን፤

4. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ በዚህ የአቋም መግለጫ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደ ተቀመጠው የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎች በዚህም ዘመን መሥራታቸውን የምናምንና የምንለማመድ መሆኑ የተረጋገጠ ነው፤ በአንጻሩ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስም የሚደረጉ ማጭበርበሮችን፥ ስጦታዎቹን የገንዘብ ማግኛ መንገድ ማድረግን፥ የተለያዩ ቁሳቁሶችን፥ ማለትም እንደ ዘይት፥ ጨው፥ ውሃ፥ ጨርቅ፥ አፈር፥ ወዘተ. “የተጸለየባቸው ናቸው” በሚል ለሽያጭ ማቅረብን፥ ለጸሎት የሚመጣ ጥያቄን በገንዘብ መደራደርን እና የመሳሰሉትን ማጭበርበሮች አጥብቀን እየተቃወምን፥ እነዚህ ልምምዶች ከእኛ ከወንጌላውያን ክርስትና አማኞች ጋር ፍጹሞ የሚቃሩንና የማይወክለን መሆኑን እንገልጻለን፤ በተጨማሪም፥ በሃይማኖት ስም የሚደረጉ ማናቸውንም ዐይነት ማጭበርበሮችን በሚመለከት ለሚነሡ ሕጋዊ ክሶች የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምንም ዐይነት ሽፋንም ሆነ ከለላ የማይሰጡ መሆኑን እናሳውቃለን፤

5. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን አምኖ የተቀበለና የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነ አማኝ ሁሉ፥ የጽድቅና የቅድስና ሕይወትን የሚለማመድ መሆኑን በጽኑ እናምናለን፤ በአንጻሩ ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና ሞራል ፍጹም በተቃራኒ የሚደረግ የኀጢአት ልምምድን፥ ማለትም አመንዝራነት፥ ግብረ ሰዶማዊነት፥ የቅድመ ጋብቻ ሩካቤ ሥጋ፥ ፍቺና ተዳጋጋሚ ጋብቻን፥ ታማኝነት ማጉደልን፥ ወዘተ. ከእኛ የወንጌላውያን ክርስትና አማኞች ጋር ፍጹም የሚቃረንና የምናወግዘው መሆኑን እንገልጻለን፤

6. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ከውጪ አገር እየመጡ የተለያዩ የኑፋቄ ትምህርት የሚያስተምሩ፥ ኢትዮጵያውያን፥ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ዜጎች መኖራቸውን ተገንዝበናል፤ በመሆኑም፥ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ከውጪ አገር ለሚመጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጤናማነታቸው ሳይረጋገጥ መድረኮቻችንን አሳልፈን እንዳንሰጥ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ተገንዝበናል፤ በተያያዘም፥ ከላይ በተገለጹት የኑፋቄ ትምህርቶች፥ ባዕዳን ልምምዶችና እና የሞራል ውድቀቶች ውስጥ ያሉ ግለ ሰቦችን የሚያበረታቱና ዕውቅና የሚሰጡ አገልጋዮች ከዚህ ተግባራቸው እንዲታቀቡ እናሳስባለን፤

7. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በርካታ የኑፋቄና የስሕተት ትምህርቶች፥ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምዶችና ሞራላዊ መሠረቶችን የሚያናጉ ሐሳቦች ከሚተላለፉባቸው መንገዶች ዋነኞቹ የብዙኀን መገናኛዎች (የቴሌቪዥን፥ የሬዲዮ፥ የኅትመት እና የማኅበራዊ ሚዲያዎች) መሆናቸውን ተገንዝበናል፤ በመሆኑም፥ የትኞቹ የብዙኀን መገናኛዎች በዚህ ችግር ውስጥ እንዳሉ በመለየት አገልጋዮችና ምእመናን እንዲጠበቁ ማድረግ እንዳለብን አጥብቀን እናምናለን፤ በተጨማሪም፥ ጤነኛው ትምህርት የሚተላለፍባቸው የብዙኀን መገናኛዎችን ማበረታታትና የወንጌላውያንን ድምፅ የሚያስተጋቡ ሌሎች የብዙኀን መገናኛዎችን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ለተግባራዊነቱ የበኩላችንን ለማድረግ ቃል እንገባለን፤

8. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ ከላይ በተጠቀሱት የተሳሳቱ የአስተምህሮ፥ የልምምድና የሞራል መንገድ ውስጥ ያሉ ቤተ እምነቶች፥ መገናኛ ብዙኀን እንዲሁም ግለ ሰቦች፥ ካሉበት የሳተ አካሄድ እንዲመለሱ በራችንን ክፍት አድርገን በክርስቲያናዊ ፍቅር ጥሪ እናደርጋለን፤ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ፈቃደኞች በማይሆኑትና በስሕተት መንገዳቸው ለመቀጠል በፈቀዱት ላይ ተገቢው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርምጃ እንዲወሰድ፥ ይህንንም የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የሥራ አመራር ቦርድና የኅብረቱ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በጋራ እንዲያስፈጽሙት ሙሉ ኀላፊነት እንሰጣለን፤

9. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ በምድራችን ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን አሁን ለደረሰችበት ችግር እኛም መሪዎቿ ተጠያቂዎች መሆናችንን እንቀበላለን፤ ይህም ሲባል በቂ እና ተገቢ ትምህርት አለመስጠታችን፥ የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታዎችን በተገቢው መንገድ አለማበረታታታችን፥ መድረካችንን ለሐሰት ትምህርቶችና ልምምዶች ክፍት ማድረጋችን እንዲሁም ስሕተቶች ሲፈጠሩ ፈጣን የእርምት ርምጃ አለመውሰዳችን፥ በጸጋ ስጦታዎች መካከል ማበላለጣችን፥ በዚህም እግዚአብሔርን ማሳዘናችንን እየተገነዘብን፥ ባለማወቅም ሆነ በአሠራር ጒድለት የተበደሉ ወይም የተጐዱ ወንድሞችና እኅቶች እንደሚኖሩ በመረዳት ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ምሕረት እንጠይቃለን፤ ከዚህም የተነሣ የተጐዱ ምእመናንን ይቅርታ እንጠይቃለን፤ ቤተ ክርስቲያን ከገባችበት አሳሳቢ ችግር እንድትወጣ ተገቢውን የንስሓና የምልጃ ጸሎት በየቤተ እምነቶቻችን እናደርጋለን፤ እውነተኛውን ትምህርት በትጋት የማስተማርና ደቀ መዝሙር የማድረግ ኀላፊነታችንን እንወጣለን፤

በየአብያተ ክርስቲያናቱ ያሉ ምእመናንም በዚህ ረገድ ለበደሉት ማናቸውም በደል ሁሉ የጌታን ምሕረት እንለምናለን።

10. እኛ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች፥ ዛሬ መጋቢት 22 ቀን 2009 ዓ.ም. ያወጣነው የአቋም መግለጫም ሆነ የኅብረቱ ጽ/ቤት ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ፊት የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ለመተግበር ቃል እየገባን፥ ይህንንም ባለን የቤተ ክርስቲያን መዋቅር መሠረት ለማስጸፈም፥ በየክልሉ ካሉ የወንጌላውያን አብያት ክርስቲያናት አደረጃጀቶች ጋር በአንድነት በመሥራት መንጋዎቻችንን የመጠበቅ ኀላፊነታችንን እንደምንወጣ እንገልጻለን፤

ይህ መግለጫ እንደየአስፈላጊነቱ ተገቢ ለሆኑ ተቋማት እና ድርጅቶች እንዲደርስ ጽ/ቤቱ እንዲሠራ እናሳስባለን።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን ይጠብቅ፤ አገራችንንም ይባርክ!

መጋቢት 22 ቀን፥ 2009 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ